## የንጥር-ጥናት አውትላይኖች
## ኢዮብ፣ ምሳሌ እና መክብብ

### ቁልፍ መግለጫዎች

እግዚአብሔር የሚወዱትን ሰዎች በማደቡ ውስጥ ያለው ዓላማ
ሰውን በመፍጠሩ ውስጥ ላለው ዓላማው መፈጸም
በእነርሱ በኩል ይገለጥ ዘንድ
ከእርሱ ውጭ የሆነውን ያጡትን የራሳቸውን ነገር ሁሉ ባለፈ መልኩ፣
እርሱን ሙሉ በሙሉ ያተርፉት ዘንድ ነው።

ኢዮብ በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በግብረገባዊነቱ ራሱን የገለጠ መልካም ሰው ነበር፣
ነገር ግን የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብ ምንም ወደ መሆን እንዲቀነስ፣
በሕልውናው እንዲጠበቅ፣ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ውስጥ እንዲካፈል፣
እና መለኮታዊዎቹን ባሕርያት በመግለጥ አምላክ-ሰው እንዲሆን ነበር።

ቅዱስ ሕዝቡን በማደቡ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ
ከሁሉ ነገር ባዶ እንዲሆኑ
እና እግዚአብሔርን ብቻ እንደ ትርፋቸው እንዲቀበሉ ነው፤
የእግዚአብሔር የልቡ መሻት ለማንነታቸው እርሱን እንደ ሕይወት፣
እንደ ሕይወት አቅርቦት እና እንደ ሁሉ ነገር በሙላት ያተርፉት ዘንድ ነው።

በእግዚአብሔር የተመረጡት እና የተዋጁት ሕዝቡ ክርስቶስን
ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ጥበብ ሲለማመዱት
እና የክርስቶስን ብልጥግናዎች ሲካፈሉ እና ሲደሰቱ፣
እነዚህ ብልጥግናዎች የእግዚአብሔር ብዙ ልዩ ልዩ ጥበብ
በሰማያት ላሉት መላእክታዊ አለቆች እና ሥልጣናት የሚታወቁባት
ቤተ ክርስቲያን አድርገው ያቀናብሯቸዋል።

© 2020 Living Stream Ministry

መልእክት አንድ

**በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ያለው ታላቁ ጥያቄ**
**እና ታላቁ መልስ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ኢዮብ 1፡1፤ 10፡2፣ 13፤ ኤፌ. 3፡9፤ ኢዮብ 42፡5-6

**I. በኢዮብ መጽሐፍ ያሉት አርባ ሁለት ምዕራፎች ሁለት ክፍል ካለው ጥያቄ ጋር ይተዉናል፡- እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ውስጥ ያለው ዓላማ ምንድነው፣ እና እግዚአብሔር የተመረጡት ሕዝቡን በማደቡ ውስጥ ያለው ዓላማ ምንድነው?—1፡1፣ 10፡2፣ 12-13፤ ተዛ. 11፡12፤ 13፡4፡-**

ሀ. ኢዮብም እግዚአብሔርን "የምትከራከረኝ ለምን እንደ ሆነ ንገረኝ" አለው (10፡2)፤ "እነዚህንም ነገሮች በልብህ ውስጥ ሰወርህ። ይህ ሁሉ በአሳብህ እንዳለ አውቃለሁ" (ቁ. 13)።

ለ. ይህ የሚያመለክተው ኢዮብ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ እንዳደረገው ምክንያቱን ሊረዳ እንዳልቻለ ነው፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የተሰወረ የሆነ ምክንያት መኖር እንዳለበት አመነ፤ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ተሰውሮ የነበረው ነገር የዘመናት ምሥጢር—ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ—ነበር—ኤፌ. 3፡9።

**II. ለዚህ ታላቅ ጥያቄ ታላቁ መልስ በእግዚአብሔር ውስጥ ለዘመናት ተሰውሮ የነበረው ምስጢር፣ ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ሲሆን ይህም ለተመረጡት ሕዝቡ ሕይወታቸው እና ባሕርያቸው ለመሆን በመለኮታዊው ሥላሴው እንደ አብ በወልድ ውስጥ በመንፈስ ወደ እነርሱ ውስጥ ራሱን ለማደል የሆነው ከልቡ መሻት ጋር የሆነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ውጥን ነው፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር ሙላት፣ ለእግዚአብሔር መገለጥ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን ሕይወታዊ አካል፣ እንደ አዲሱ ሰው የክርስቶስን አካል ይሆኑ ዘንድ ነው—1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 3፡9፣ 19፤ ዘፍ. 1፡26፤ ኢሳ. 43፡7፤ ሮሜ 8፡29፤ 1 ዮሐ. 3፡2፡-**

ሀ. ኢዮብ እና ባልንጀሮቹ እያለፈበት ያለው መከራ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሆነ አሰቡ፤ ሆኖም ግን፣ የኢዮብ መከራዎች የእግዚአብሔር ፍርድ ሳይሆኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን አብዝቶ ያተርፍ ዘንድ የእግዚአብሔር ኢዮብን መግፈፍ እና መጨረስ ነበሩ።

ለ. ምንም እንኳን እግዚአብሔር ኢዮብን ቢገፍፈውም በኢዮብ አልተናደደም ነበር፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር ኢዮብን የቅርብ ወዳጁ እንጂ ጠላቱ አድርጎ አልቆጠረውም ነበር—ኢዮብ 19፡11፤ ተዛ. 10፡13።

ሐ. ኢዮብ በመከራ ጊዜ ውስጥ ካለፈ በኋላ ለእግዚአብሔር መገለጥ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ለማሟላት ሌላ ሰው—አዲስ ሰው፣ አዲስ ፍጥረት (ገላ. 6፡15) ይሆን ዘንድ በመለኮታዊው ሥላሴ እንደገና እንደሚገነባ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር (2 ቆሮ. 5፡17)፤ ይህ በኢዮብ መጽሐፍ ላለው ለታላቁ ጥያቄ ታላቁ መልስ ነው።

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ለመለኮታዊው እደላ በሆነው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን፤ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ካላወቅን መጽሐፍ ቅዱስን አንረዳም፤ በኢዮብ ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብን በመለኮታዊው ኢኮኖሚው መሠረት በእግዚአብሔር የተቀናበረ የእግዚአብሔር ሰው ማድረግ ነበር፡-

1. ስልሳ ስድስት መጽሐፍት ያሉት መጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ ነገር ብቻ ነው፡- ክርስቶስን እንኖረው እና ክርስቶስን እንገልጠው ዘንድ እግዚአብሔር ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ሁሉ ነገራችን ለመሆን በክርስቶስ በመንፈስ ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ማደሉ፤ ይህ ሕይወታችንን የሚገዛ መርህ መሆን አለበት—ዮሐ. 10፡10፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡2፣ 10፣ 6፣ 11፤ ፊልጵ. 1፡19-21፤ 2 ቆሮ. 3፡6።
2. እግዚአብሔር ኢዮብን ማደቡ በስነ-ምግባር ፍጹምነትን ከመፈለግ፣ በሌላ በምንም ነገር ፈንታ እግዚአብሔርን ወደ መፈለግ እና ወደ ማትረፍ ፍለጋ ውስጥ ይዞር ዘንድ ከስነ-ምግባር ክልል ውስጥ አውጥቶ ወደ እግዚአብሔርን-ማትረፊያ ክልል ውስጥ እርሱን ለማምጣት ነበር፤ በእግዚአብሔር ፊት ሰው ያለው ስፍራ የሚመሠረተው ባተረፈው የእግዚአብሔር መጠን ነው—መዝ. 27፡8፤ 105፡4፤ ፊልጵ. 3፡8፤ ማቴ. 25፡3-4፣ 9፤ ምሳ. 23፡23፤ ራእ. 3፡18፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ 4፡17፤ 1 ጴጥ. 2፡7፤ ዳን. 5፡27፤ 9፡23፤ 10፡11፣ 19።
3. ቅዱስ የሆነውን ሕዝቡ በማደቡ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ ከሁሉ ነገር ባዶ ይሆኑና እግዚአብሔርን ብቻ እንደ ትርፋቸው ይቀበሉ ዘንድ ነው፤ እግዚአብሔር ሕዝቡ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ይሆኑ ዘንድ ድስታቸው ወደ ሙሉ መጠን እስኪደርስ ድረስ ከሌሎች ነገሮች ሁሉ ይልቅ እርሱን ጨምረው ጨምረው እንዲያተርፉት፣ እንዲካፈሉት፣ የራሳቸው እንዲያደርጉት እና እንዲደሰቱት ይፈልጋል—ማቴ. 5፡3፤ መዝ. 43፡4፤ 73፡25-26፤ ፊልጵ. 3፡8-9፤ ራእ. 21፡2።

4. ሰውን በመፍጠሩ እና የተመረጡት ሕዝቡን በማደቡ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በተመለከተ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ እንዳለ እንደ የታላቁ ጥያቄ ታላቁ መልስ የመላው አዲስ ኪዳን ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ይህ ነው።

III. **የኢዮብ መሠረታዊ ችግር የእግዚአብሔር እጥረት ስለነበረበት ነው፤ ከኢዮብ ጋር በነበሩት የእግዚአብሔር ባደቦች ውስጥ ሁሉ የነበረው የእግዚአብሔር ውጥን ራሱን ወደ ኢዮብ ውስጥ ለማካፈል ጊዜ ይኖረው ዘንድ የኢዮብን ሕልውና በመጠበቅ (2፥6) ኢዮብን ምንም ወደ መሆን መቀነስ ነበር፤ እግዚአብሔር ግድ የሚሰኘው ለአንድ ነገር ብቻ ነው—እርሱ ወደ እኛ ውስጥ ለመሠራቱ (ኤፌ. 3፥16-19)፦**

ሀ. ኢዮብ የራሱ-ጽድቅ ነበረው (ኢዮብ 6፥30፤ 9፥20፤ 27፥5-6፤ 32፥1)፣ በማንነቱ ሊሆን በቻለው ረክቶ ነበር (13፥3፤ 23፥3-4፤ 31፥6)፣ ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ፊት የገዛ ራሱን አሳዛኝ ሁኔታ አያውቅም ነበር (ተዛ. ራእ. 3፥16-18)።

ለ. የኢዮብ ክብር የገዛ ፍጹምነቱ እና ቅንነቱ ነበር፣ አክሊሉም ግብረገባዊነቱ ነበር፤ እግዚአብሔር ክብሩን ከኢዮብ ገፎበት አክሊሉንም ከኢዮብ ራስ ላይ ወስዶበት ነበር (ኢዮብ 19፥9)፤ የኢዮብ ተስፋ የግብረገባዊነቱን “ዛፍ” መገንባት ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ ያለው ዛፍ በኢዮብ ውስጥ እንዲያድግ አልፈቀደም ነበር፤ ይልቁንም እግዚአብሔርን ወደሚያተርፍበት ክልል ውስጥ ኢዮብ ይገባ ዘንድ እግዚአብሔር ይህን ዛፍ፣ ይህን ተስፋ (ቁ. 10) ነቀለው።

ሐ. ኢዮብ በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ እንዳለ ሰው በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በግብረገባዊነቱ ራሱን በሚገነባበት የተሳሳተ ክልል ውስጥ እንደነበር ያውቅ ዘንድ እግዚአብሔር ፈለገ፤ ኢዮብ በእነዚህ ነገሮች ራሱን አከበረ፣ እግዚአብሔር ግን እነዚህን መገፈፍ እንደሚገባቸው እንቅፋቶች ቆጠራቸው ይኸውም ኢዮብ እግዚአብሔርን በባሕሪው፣ በሕይወቱ፣ በንጥረ-ነገሩ እና በውስጠ-ነገሩ መቀበል እና በዚህም አምላክ-ሰው፣ እግዚአብሔርን የሚገልጥ እና እርሱን ወደ ሌሎች ውስጥ የሚያድል በአዲሱ ፍጥረት ውስጥ ያለ ሰው ለመሆን በገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ መለወጥ ይችል ዘንድ ነው—2 ቆሮ. 3፥18፤ 1 ጴጥ. 4፥10፤ ኤፌ. 3፥2።

መ. እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ የነበረው ውጥን በእግዚአብሔር ተፈጥሮ እና ባሕርያት የታደሰ ኢዮብ ይገነባ ዘንድ በነበረው ፍጹምነት እና ቅንነት ፍጥረታዊውን ኢዮብ ማፈራረስ ነበር፤ የመንፈስ ቅዱስ ቅጣት የታደሰ ማንነትን ለማቀናበር ፍጥረታዊ ማንነታችንን ያፈራርሳል—2 ቆሮ. 4፥16-18፤ ሮሜ 8፥28-29።

ሠ. በውስጣችን ያለው የመንፈስ ሥራ ለእኛ አዲስ ማንነትን ማቀናበር ሲሆን ከውጭ ያለው የመንፈስ ሥራ ደግሞ በከባቢ ሁኔታችን አማካኝነት የፍጥረታዊ ማንነታችንን እያንዳንዱን ገጽታ ማፈራረስ ነው፤ ከሚሠራው መንፈስ ጋር መተባበር እና እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን ከባቢ ሁኔታ መቀበል አለብን—ፊልጵ. 4፥12፤ ኤፌ. 3፥1፤ 4፥1፤ 6፥20፤ 1 ቆሮ. 7፥24።

ረ. በዚህ አጽናፍ-ዓለም፣ በተለይ ደግሞ ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር በተገናኘ፣ መከራን የመቀበል ዋነኛው ዓላማ ሰው እግዚአብሔርን በሙሉ መጠን ማትረፍ ይችል ዘንድ [በመከራ] በኩል የእግዚአብሔር የራሱ ባሕርይ ወደ ሰው ባሕርይ ውስጥ እንዲሠራ ነው—2 ቆሮ. 1፥8-9፤ 4፥16፦

1. ሕያው የሆነው እግዚአብሔር በሰው ቦታ ብዙ ድርጊቶችን መፈጸም ሲችል ሳለ፣ ሕያው የሆነው እግዚአብሔር ሕይወት እና ባሕርይ ወደ ሰው ውስጥ አልተሠሩም፤ የትንሣኤ አምላክ ሲሠራ፣ ሕይወቱ እና ባሕርይው ወደ ሰው ውስጥ ይሠራሉ—ቁ. 16።
2. እግዚአብሔር በውጫዊ ድርጊቶች ኃይሉ ይታወቅ ዘንድ እየሠራ ሳይሆን ራሱን ወደ ሰው ውስጥ ለማካፈል እና ለመሥራት እየሠራ ነው፤ እግዚአብሔር ሕይወቱን እና ባሕሪውን ወደ ውስጣችን ለመሥራት ከባቢ ሁኔታዎችን ይጠቀማል—ገላ. 4፥19፤ 2 ቆሮ. 4፥7-12፤ 1 ተሰ. 3፥3፤ ዮሐ. 16፥33።
3. በትንሣኤ ውስጥ ለመኖር እና በትንሣኤው አምላክ ለመቀናበር በ”ነገር ሁሉ” የእግዚአብሔር በኩር ልጅ የሆነውን የክርስቶስን መልክ መምሰል አለብን—ሮሜ 8፥28-29፤ ዕብ. 12፥10፤ ተዛ. ኤር. 48፥11።
4. በመከራዎች ውስጥ ስናልፍ ለእግዚአብሔር ቅሬታችንን እናቀርብ ይሆናል፣ ነገር ግን ቅሬታችን ምርጡ ጸሎት፣ ለእግዚአብሔር እጅጉን ደስ የሚያሰኝ ጸሎት ሊሆን ይችላል፤ ቅሬታችንን ስናቀርብ ሳለን እግዚአብሔር ደስ እየተሰኘ ነው፣ ምክንያቱም የበኩር ልጁን መልክ እንመስል ዘንድ ነገር ሁሉ በአንድ ላይ ለበጎ እንዲሠራ እያደረገ ነውና—ተዛ. መዝ. 102፣ ርዕስ።

IV. **ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡን ለማግኘት ለኢኮኖሚው መፈጸም ሰውን መለኮት የማድረግ የሦስታንዱ አምላክ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ መለኮታዊው መንፈስ ከሰው መንፈሳችን ጋር እንደ አንድ በተዋሐደበት፣ በተዋሐደው መንፈስ ውስጥ ነው—1 ቆሮ. 6፥17፤ ራእ. 1፥10፤ 4፥2፤ 17፥3፤ 21፥10፤ ተዛ. ኢዮብ 12፥10፤ 32፥8፦**

ሀ. በክርስትና ሕይወታችን በመንፈስ መኖር እና በመንፈስ መመላለስ አለብን፤ የምናደርገውን ነገር ሁሉ እና የምንሆነውን ነገር ሁሉ በመንፈስ፣ ከመንፈስ ጋር፣ በመንፈስ ውስጥ እና በመንፈስ በኩል ማድረግና መሆን አለብን፤ ስለዚህ

የመለኮታዊውን መንፈስ በእኛ ውስጥ መኖር፣ በእኛ ውስጥ ቤቱን መሥራት እና እኛን መለወጡን ለመለማመድ የምናደርገውን ነገር ሁሉ መንፈሳችንን እያንቀሳቀስን በማድረግ መንፈሳችንን መንከባከብ ያስፈልገናል—ገላ. 5፡16፣ 25፤ ፊልጵ. 3፡3፤ ሮሜ 8፡4፣ 6፤ 2 ቆሮ. 2፡12-14፤ ሚል. 2፡15-16።

ለ. ሁሉን-ካካተተው መንፈስ ውጭ ምንም አይነት ድርጊት መፈጸም የለብንም፤ ከመንፈስ ውጭ ምንም አይነት ሁኔታ መጋፈጥ ወይም ምንም አይነት ፍላጎትን መሙላት የለብንም፤ መለኮታዊውን መንፈስ በመንፈሳችን መንካትን መማር አለብን፤ ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም ይህ የክርስቲያን ሕይወት እና የክርስቲያን ሥራ ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ነው—ዘካ. 4፡6፤ 2 ቆሮ. 3፡3፣ 6፤ ሮሜ 1፡9፤ 7፡6፤ ፊልጵ. 3፡3።

ሐ. ክርስቲያን እና ድል ነሺ መሆን አስቸጋሪ ብቻ አይደለም—የማይቻል ነው፤ በእኛ ውስጥ ሁሉን-እንዳካተተው መንፈስ በመንፈሳችን የሚኖረው፣ በሂደት ያለፈው እና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ብቻ ነው ክርስቲያን እና ድል ነሺ መሆን የሚችለው—ሉቃ. 1፡37-38፤ 2 ቆሮ. 4፡13፤ ሮሜ 8፡2።

መ. የምናደርገውን ነገር ሁሉ በመንፈስ መሠረት እስካደረግን ድረስ፣ የክርስቶስን ተሠግዎ፣ የስብዕና ኑሮ፣ ሞት፣ ትንሣኤ እና ዕርገት ከመንፈስ መፍሰስ ጋር መለማመድ እንችላለን፤ ይህ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስን አካል፣ አዲሱን ሰው እና እንደ የሦስታንዱ አምላክ ሕይወታዊ አካል የወይን ተክሉንና ቅርንጫፎቹን ያደርገናል—ፊልጵ. 1፡19፤ ኢዮኤል 2፡28-32፤ ሐዋ. 2፡16-21፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡15፤ 4፡4፣ 23-24፤ ዮሐ. 15፡1-11፤ ራእ. 3፡12፤ 19፡7-9፤ 21፡2፣ 10።

**V. ኢዮብ በግል ልምምዱ እና ራሱን በመጸየፉ ውስጥ እግዚአብሔርን በማትረፍ እግዚአብሔር ለኢዮብ በመገለጡ ኢዮብ እግዚአብሔርን አየ—ኢዮብ 38፡1-3፤ 42፡1-6፡-**

ሀ. በሂደት እንዳለፈው እና እንደተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ዛሬ አምላካችን ሁሉን-ያካተተው መንፈስ ነው፤ ዛሬ የምናየው አምላክ የተጠናቀቀው መንፈስ ነው፣ እርሱንም በመንፈሳችን ውስጥ ልናየው እንችላለን—2 ቆሮ. 2፡10፤ 2 ጢሞ. 4፡22።

1. በእግዚአብሔር ለመቀናበር እግዚአብሔርን እናያለን፤ እግዚአብሔርን ማየት ይለውጠናል፣ እግዚአብሔርን ማየት ደግሞ እግዚአብሔርን ከማትረፍ ጋር እኩል ነው—2 ቆሮ. 3፡16፣ 18፤ ማቴ. 5፡8፤ ራእ. 22፡4።
2. እግዚአብሔርን አብዝተን ስናየው እና ስንወደው፤ አብዝተን ራሳችንን እንክዳለን፣ ራሳችንን እንጠላለን—ኢዮብ 42፡5-6፤ ኢሳ. 6፡5፤ ሉቃ. 14፡26።

ለ. እግዚአብሔርን ለማየት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ አለብን—ኤፌ. 1፡17-18፤ 3፡16-17፤ 1 ቆሮ. 2፡9-16፤ 2 ቆሮ. 4፡13፤ 1 ጢሞ. 4፡7፤ 2ጢሞ 1፡6-7፡-

1. እርሱን በመንፈሳችን ውስጥ አብዝተን ስናየው፣ እንደ የውስጥ አቅርቦታችን ንጥረ-ነገሮቹን ሁሉ አብዝተን እንቀበላለን—2 ቆሮ. 3፡16-18።
2. በመከራዎቻችን ውስጥ ጌታን እንደ ማደሪያ ስፍራችን፣ እርሱን ለእኛ አጥጋቢ (በቂ) እንደሆነ ምሥጢራችን አድርገን በመውሰድ ለመንፈሳችን መጠንቀቅ እና ትኩረት መስጠት አለብን—2፡13፤ 7፡5-6፤ ሚል. 2፡15-16፤ መዝ. 91፡1፤ ፊልጵ. 4፡11-13፤ መዝ. 90፡1-12፤ 31፡20፤ ኢሳ. 32፡2።

ሐ. እግዚአብሔርን ለማየት ልባችንን ማስተካከል አለብን—2 ቆሮ. 3፡16፣ 18፤ ማቴ. 5፡8፤ 13፡18-23፡-

1. በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል እንደገና በመቀናበር በእግዚአብሔር ቃል አቅጣጫ ለመያዝ፣ ለመገዛት፣ ለመመራት እና [በእግዚአብሔር ቃል] ቁጥጥር ሥር ለመሆን በአእምሯችን መንፈስ መታደስ አለብን—ኤፌ. 4፡23፤ ዘዳ. 17፡18-20፤ ፊልጵ. 2፡2፣ 5።
2. ለቤቱ እንደሚሆን ቅናት በእርሱ የተሞላ ስሜት ይዘን በጌታ ፍቅር እሳት መቀጣጠል አለብን—1፡8፤ 2 ቆሮ. 5፡14፤ 2 ጢሞ. 1፡6-7፤ ዮሐ. 2፡17፤ ማር. 12፡30።
3. በመከራዎች ውስጥ ፈቃዳችን ለክርስቶስ ራስነት ይገዛ ዘንድ በክርስቶስ መሸነፍ እና በክርስቶስ መለወጥ አለበት (ፊልጵ. 2፡13፤ ተዛ. መኃ. 4፡1፣ 4፤ 7፡4፣ 5)፣ እና ወድ በሆነው፣ በሚያነጻው እና በሚያጠራው የክርስቶስ ደም በጎ እና ንጹህ ሕሊናን መጠበቅ አለብን (ሐዋ. 24፡16፤ 1 ጢሞ. 3፡9፤ ዕብ. 9፡14፤ 10፡22)።

**VI. እግዚአብሔር የሚወዱትን ሰዎች በማደቡ ውስጥ ያለው ዓላማ ሰውን በመፍጠሩ ውስጥ ላለው ዓላማው መፈጸም በእነርሱ በኩል ይገለጥ ዘንድ (ዘፍ 1፡26) ከእርሱ ውጭ የሆነውን ያጡትን የራሳቸውን ነገር ሁሉ ባለፈ መልኩ፣ እርሱን ሙሉ በሙሉ ያተርፉት ዘንድ ነው (ፊልጵ. 3፡7-8)።**

*© 2020 Living Stream Ministry*